https://www.path-2-happiness.com/am

الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness

https://www.path-2-happiness.com/am

የዩኒቨርስና የሰው ልጅ መፈጠር . . ጥበቡ ክቡርነቱና ግቡ

ማውጫ

የዩኒቨርስና የሰው ልጅ መፈጠር . . ጥበቡ ክቡርነቱና ግቡ

ስለ ዩኒቨርስ አፈጣጠር አስበው ያውቃሉ?!
ከዩኒቨርስ መፈጠር ጀርባ ያለው ጥበብ
ሰውን መፍጠሩና ክቡር ፍጡር ማድረጉ ሴትን ከወንድ ጋር እኩል ማድረግ
የሰው ልጅ መፈጠር ዓላማውና ምስጢሩ
ሰው ሆይ! ከዚህ በኋላስ . .



የዩኒቨርስና የሰው ልጅ መፈጠር . . ጥበቡ ክቡርነቱና ግቡ

https://www.path-2-happiness.com/am

ስለ ዩኒቨርስ አፈጣጠር አስበው ያውቃሉ?!

አላህ (ሱ.ወ.) የፈጠራቸውን ፍጥረታት ማስተዋልና ማስተንተን ወደ እምነት ከሚጠሩ፣ለሰው ልጅ እርግጠኝነትን ከሚጨምሩ፣የፈጣሪን ኃያልነትና የላቀ ጥበቡን ከሚያሳውቁት ዋነኛ መሳሪያዎች አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ٤٤} [العنكبوت: ٤٤].

‹‹አላህ ሰማያትንና ምድርን እውነተኛ ኾኖ ፈጠረ፣በዚህ ውስጥ ለምእመናን ታምር አለበት።›› [አል ዐንከቡት፡44]

በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፍጥረታት ይገኛሉ። ለመሆኑ እነዚህን ሁሉ ከመፍጠር ጀርባ ያለው ጥበብ ምን ይሆን?!

ኦ አምላኬ!

‹‹የዘመናዊውን ስነፈለክ አንዳንድ ፎቶግራፎች ባየሁ ጊዜ የመጀመሪያ መስተጋብሬ ፦ ኦ አምላኬ! ሥራው ሙሉ በሙሉ ተሳክቷል፣በሞቱ እጹብ ድንቅ ነገር ነው ብዬ መጮኽ ነበር።››

ፓውል ሞርዲን
በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ
የስነፈለክ ፕሮፌሶር

የአላህ (ሱ.ወ.) ገደብ የለሽ ችሎታና የኃያልነቱ ማስረጃዎች የምንጸባረቁባቸው አስደማሚ ምልክቶች በዩኒቨርስ ውስጥ ይገኛሉ። ዘመናዊው ሳይንስ የዚህን ጥበበኛ ኃያል ፈጣሪ ታላቅነት የሰውን ልጅ እንዲገነዘብ የሚያደርጉ አስረጅ ምልክቶችንንና ግኝቶችን ማቅረቡን እንደቀጠለ ይገኛል።

የሰው ልጅ ይህን ዩኒቨርስና ያቀፋቸውን ፍጥረታት በጥልቀት ቢያስተውል፣እጅግ በረቀቀ ገደብ የለሽ ኃያል ችሎታ የተፈጠረ፣አቅዶ ወስኖና አቀነባብሮ ባኖረው ጥበበኛ ዐዋቂ አምላክ የተገኘ መሆኑን በፍጹምነት አረጋግጦ ይቀበላል። ይህ ዩኒቨርስና ጠፈራዊ አካላቱ፣ከዋክብቱ፣የፀሐያዊ ጭፍራ ስርዓቱና ያካተታቸው ፕላኔቶቹ፣መሬትና በሕሮቿ፣ወንዞቸዋ፣ተራሮቸዋ፣እንስሳቱ፣እጽዋቱ . . እነዚህን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ.) ከምንም ፈጥሮ ያስገኛቸው መሆኑን ማስተንተኑ ብቻ የአላህ (ሱ.ወ.) ችሎታ ዕውቀቱና ጥበቡ ምን ያህል ኃያል እንደሆነ ለመገንዘብ በቂ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَوَ لَمۡ يَرَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ كَانَتَا رَتۡقٗا فَفَتَقۡنَٰهُمَاۖ وَجَعَلۡنَا مِنَ ٱلۡمَآءِ كُلَّ شَيۡءٍ حَيٍّۚ أَفَلَا يُؤۡمِنُونَ ٣٠ وَجَعَلۡنَا فِي ٱلۡأَرۡضِ رَوَٰسِيَ أَن تَمِيدَ بِهِمۡ وَجَعَلۡنَا فِيهَا فِجَاجٗا سُبُلٗا لَّعَلَّهُمۡ يَهۡتَدُونَ ٣١ وَجَعَلۡنَا ٱلسَّمَآءَ سَقۡفٗا مَّحۡفُوظٗاۖ وَهُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِهَا مُعۡرِضُونَ ٣٢ وَهُوَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ كُلّٞ فِي فَلَكٖ يَسۡبَحُونَ ٣٣} [الأنبياء: ٣٠- ٣٣]

‹‹እነዚያም የካዱት ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መኾናችንን አያውቁምን? ሕያው የኾነንም ሁሉ ከውሃ ፈጠርን፣አያምኑምን? በምድርም ውስጥ በነሱ እንዳታረገርግ ጋራዎችን አደረግን፣ይመሩም ዘንድ በርሷ ውስጥ ሰፋፊ መንገዶችን አደረግን። ሰማይንም (ከመውደቅ) የተጠበቀ ጣራ አደረግን፣እነሱም ከታምራቶቿ ዘንጊዎች ናቸው። እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ፀሐይና ጨረቃንም የፈጠረ ነው፣ሁሉም በፈለካቸው (መዞሪያቸው) ውስጥ ይዋኛሉ።››[አልአንቢያ፡30-33]

አስተዋይ ሰው የአላህን ፍጡራን ሲያስተውል በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ፍጥረት ሁሉ የጌታው አምላኪ መሆኑን፣ፍጥረታቱ በመላ እርሱን የሚያወድሱና የሚያጠሩት መሆኑን በእርግጠኝነት ይረዳል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ ٱلۡمَلِكِ ٱلۡقُدُّوسِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَكِيمِ ١} [الجمعة: ١]،

‹‹በሰማያት ያለው፣በምድርም ያለው ሁሉ ለአላህ፣ንጉሥ ቅዱስ አሸናፊ ጥበበኛ ለኾነው ያሞግሳሉ።›› [አል ጁሙዓህ፡1]

ለኃያልነቱም ይሰግዳሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسۡجُدُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ وَٱلۡجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٞ مِّنَ ٱلنَّاسِۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيۡهِ ٱلۡعَذَابُۗ وَمَن يُهِنِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِن مُّكۡرِمٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَفۡعَلُ مَا يَشَآءُ ١٨} [الحج:18].

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹አላህ በሰማያት ያለው ሁሉ፣በምድርም ያለው ሁሉ፣ፀሐይና ጨረቃም ፣ከዋክብትም፣ተራሮችም፣ዛፎችም፣ተንቀሳቃሾችም፣ከሰዎች ብዙዎችም፣ለርሱ የሚሰግዱለት መኾኑን አታውቁምን? ብዙውም በርሱ ላይ ቅጣት ተረጋገጠበት፣አላህ የሚያዋርደውም ሰው ለርሱ ምንም አክባሪ የለውም፣አላህ የሻውን ይሠራልና።››[አል ሐጅ፡118]

በዚህ መልኩም ፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪያቸውን ያወድሳሉ፣ይሰግዱለታልም። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلطَّيۡرُ صَٰٓفَّٰتٖۖ كُلّٞ قَدۡ عَلِمَ صَلَاتَهُۥ وَتَسۡبِيحَهُۥۗ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِمَا يَفۡعَلُونَ ٤١} [النور: ٤١]

‹‹አላህ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ፣በራሪዎችም ክንፎቻቸውን (በአየር ላይ) ያንሳፈፉ ኾነው፣ለርሱ የሚያጠሩ (የሚያወድሱ) መኾናቸውን አላወቅህምን? ሁሉም ስግደቱንና ማጥራቱን በእርግጥ ዐወቀ፣አላህም የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።››[አል ኑር፡41]

እናም ለአማኝ ሰው መላው ዩኒቨርስ በጥቅሉ በአንድ ቅፍለት ወደ አንድ አቅጣጫ ወደ አላህ (ሱ.ወ.) እያመራ መሆኑ ይታየዋል። እርሱም በበኩሉ ከዚህ ብሩክ መልካም ጉዞ ጋር ራሱን ያጣጥምና ሕይወቱ አስደሳች ሆኖ ውስጣዊ መረጋጋት ያገኛል።

ከመለኮታዊ ማስረጃዎች አንዱ ነው

‹‹የኛዋን ፕላኔት መመልከቱ ከመለኮታዊ ማስረጃዎች አንዱ ነበር።››

ኤድጋር ሚሼል

ጨረቃ ገጽ ላይ በመራመድ ስድስተኛው ሰው

ይህ የአላህ መፍጠር ነው!!

‹‹ይህን ነገር ማየት ብቻ የሰውን ልጅ ሊለውጥ ይገባል። አንድ ሰው ስለ ዩኒቨርሱ ሲናገር ለአላህ ፍጥረተ ዓለምና ለአላህ ፍቅር ታላቅ ከበሬታ እንዲኖረው ሊያደርገው ይገባል።››

ጆምስ ኤሮዊን

የሕዋ ተጓዥ

አላህ ሰውን ክቡር ፍጡር ማድረጉ

‹‹የአላህ ሕግ የሆነው እስላም በዙሪያችን ስላለው ተፈጥሮ ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን። ተራሮች፣ባሕሮች፣ፕላኔቶችና ከዋክብት በአላህ ትእዛዝ ብቻ ይሄዳሉ፣በጉዞአቸውም በርሱ ብቻ ይመራሉ። ሁሉም ለፈጣሪያቸው ትእዛዝ ተገዥዎች ናቸው። በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለችው እያንዳንዷ አቶም ግሉዝ አካላትን ጨምሮ እንደዚሁ የግድ ለርሱ ታዛዦችና ተገዥዎች ናቸው። የሰው ልጅ ግን አላህ የመምረጥ ነጻነት የሰጠው በመሆኑ ከዚህ አጠቃላይ ሕግ ለየት ይላል። እናም ለአላህ ትእዛዝት የመገዛት ወይም የራሱን ሕግ ለገዛ ራሱ ደንግጎ በመረጠው እምነቱ መሰረት የመኖር ምርጫ አለው። የሚያሳዝነው ግን በአብዛኛው ሁኔታ ሁለተኛውን መንገድ የመረጠ መሆኑ ነው።››

ዲቦ ራፖርተር

የአሜሪካ ጋዜጣ

ከዩኒቨርስ መፈጠር ጀርባ ያለው ጥበብ

1- ለአላህ አንድነት አስረጅ መሆኑ፦

ወሰን የሌለው ይህ ዩኒቨርስ፣ያቀፋቸው ፍጥረታትና ታምራት ለአላህ (ሱ.ወ.) ኃያል ችሎታና ለድንቅ ጥበቡ ምሉእነት ትልቁ ማስረጃ ነው። አንድነቱን፣ከርሱ በቀር ሌላ አምላክና ሌላ ጌታ አለመኖሩንም በግልጽ ያመለክታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ إِذَآ أَنتُم بَشَرٞ تَنتَشِرُونَ ٢٠ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَ لَكُم مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ أَزۡوَٰجٗا لِّتَسۡكُنُوٓاْ إِلَيۡهَا وَجَعَلَ بَيۡنَكُم مَّوَدَّةٗ وَرَحۡمَةً إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٢١ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ خَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفُ أَلۡسِنَتِكُمۡ وَأَلۡوَٰنِكُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡعَٰلِمِينَ ٢٢ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ مَنَامُكُم بِٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱبۡتِغَآؤُكُم مِّن فَضۡلِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَسۡمَعُونَ ٢٣ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ يُرِيكُمُ ٱلۡبَرۡقَ خَوۡفٗا وَطَمَعٗا وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَيُحۡيِۦ بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَآۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ٢٤ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَن تَقُومَ ٱلسَّمَآءُ وَٱلۡأَرۡضُ بِأَمۡرِهِۦۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمۡ دَعۡوَةٗ مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ إِذَآ أَنتُمۡ تَخۡرُجُونَ ٢٥ وَلَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ كُلّٞ لَّهُۥ قَٰنِتُونَ ٢٦} [الروم: ٢٠- ٢٦].

‹‹እናንተንም ከዐፈር መፍጥሩ፣ከዚያም እናንተ ወዲያውኑ የምትበታተኑ ሰዎች መኾናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። ለናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ፣ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፣በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ። ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣የቋንቋዎቻችሁና የመልክቾቻችሁም መለያየት ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፣በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ታምራቶች አሉበት። በሌሊትና በቀንም መተኛታችሁ፣ከችሮታውም መፈለጋችሁ፣ከምልክቶቹ ነው፣በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች ታምራቶች አሉበት።››[አል ሩም፡30-23]

https://www.path-2-happiness.com/am

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ وَسَلَٰمٌ عَلَىٰ عِبَادِهِ ٱلَّذِينَ ٱصۡطَفَىٰٓۗ ءَآللَّهُ خَيۡرٌ أَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٥٩﴾ أَمَّنۡ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَنۢبَتۡنَا بِهِۦ حَدَآئِقَ ذَاتَ بَهۡجَةٖ مَّا كَانَ لَكُمۡ أَن تُنۢبِتُواْ شَجَرَهَآۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ بَلۡ هُمۡ قَوۡمٞ يَعۡدِلُونَ ﴿٦٠﴾ أَمَّن جَعَلَ ٱلۡأَرۡضَ قَرَارٗا وَجَعَلَ خِلَٰلَهَآ أَنۡهَٰرٗا وَجَعَلَ لَهَا رَوَٰسِيَ وَجَعَلَ بَيۡنَ ٱلۡبَحۡرَيۡنِ حَاجِزًاۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٦١﴾ أَمَّن يُجِيبُ ٱلۡمُضۡطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكۡشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجۡعَلُكُمۡ خُلَفَآءَ ٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴿٦٢﴾ أَمَّن يَهۡدِيكُمۡ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَمَن يُرۡسِلُ ٱلرِّيَٰحَ بُشۡرَۢا بَيۡنَ يَدَيۡ رَحۡمَتِهِۦٓۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ تَعَٰلَى ٱللَّهُ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٦٣﴾ أَمَّن يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَمَن يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٦٤﴾} [النمل: ٥٩- ٦٤].

‹‹(ሙሐመድ ሆይ) በል ፦ ምስጋና ለአላህ ይግባው፤በነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሰላም ይውረድ፤አላህ በላጭ ነውን? ወይስ ያ የሚያጋሩት? (ጣዖት)። ወይም ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረና ከሰማይም ለናንተ ውሃን ያወረደው? (ይበልጣል? ወይስ ያ የሚያጋሩት?)፤ በርሱም ባለ ውበት የኾኑትን የታጠሩ አትክልቶችን፣ዛፍዋን ልታበቅሉ ለናንተ ችሎታ ያልነበራችሁን አበቀልን፤ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? (የለም)፤ግን እነሱ (ከውነት) የሚያዘነብሉ ሕዝቦች ናቸው። ወይም ያ ምድርን መርጊያ ያደረገና በመካከሏም ወንዞችን ያደረገ፣ለርሷም ጋራዎችን ያደረገ፣በሁለቱ ባሕሮችም (በጣፋጩና በጨው ባሕር) መካከል ግርዶን ያደረገ፤(ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም። ወይም ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣መከራንም የሚያስወግድ፣በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደርጋችሁ፤(ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትንም አትገሠጹም። ወይም ያ በየብስና በባሕር ጨለማዎች ውስጥ የሚመራችሁ፣ነፋሶችንም ከዝናሙ በፊት አብሳሪ ኾነው የሚልክ? (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? አላህ (በርሱ) ከሚያጋሩዋቸው ሁሉ ላቀ። ወይም ያ መፍጠርን የሚጀምር፣ከዚያም የሚመልሰው፣ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አምላክ፣(ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? እውነተኞች እንደ ኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው።››[አል ነምል፡59-64]

2- ዩኒቨርስን ለሰው ልጅ የተገራ ማድረጉ፦

አላህ (ሱ.ወ.) የሰውን ልጅ ለቁሳዊ ነገሮች ተገዥ ከመሆን ነጻ አውጥቶት፣በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለውን ሁሉ፣በሰማያትና በምድርም ያለውን ከርሱ ብቻ በሆነ ችሮታና ቸርነቱ ለሰው ጥቅም የተገራና የተመቻቸ እንዲሆን አድርጎለታል። ይህም የሰው ልጅ ምድርን እንዲያለማና የተጠሪነት ግዴታውን ማለትም ለርሱ ያለው ተገዥነት ምሉእ ሆኖ ተልእኮው እንዲሳካ ለማድረግ ነው። መግራትና ማመቻቸት ማለት እዚህ ላይ ሁለት ትርጉሞች አሉት፦ አንደኛው አላህን (ሱ.ወ.)፣ችሮታውን፣ቸርነቱንና ኃያልነቱን ማወቅን መግራት ሲሆን፣ሌላው የሰውን ልጅ ለርሱ ከተገዢለት ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በላይ ደረጃውን ከፍ በማድረግ መግራትና ማመቻቸት ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُ} [الجاثية: ١٣]،

‹‹ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፣በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ታምራት አለበት።››[አል ጃሢያህ፡13]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزۡقٗا لَّكُمۡۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡفُلۡكَ لِتَجۡرِيَ فِي ٱلۡبَحۡرِ بِأَمۡرِهِۦۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡأَنۡهَٰرَ ﴿٣٢﴾ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ دَآئِبَيۡنِۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ﴿٣٣﴾ وَءَاتَىٰكُم مِّن كُلِّ مَا سَأَلۡتُمُوهُۚ وَإِن تَعُدُّواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحۡصُوهَآۗ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَظَلُومٞ كَفَّارٞ ﴿٣٤﴾} [إبراهيم: ٣٢- ٣٤]

‹‹አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣ከሰማይም ውሃን ያወረደ፣በርሱም ከፍሬዎች ሲሳይን ለናንተ ያወጣ፣መርከቦችንም በፈቃዱ በባሕር ላይ ይንሻለሉ ዘንድ ለናንተ የገራ፣ ወንዞችንም ለናንተ የገራ ነው። ፀሐይንና ጨረቃንም ዘውትር ኼያጆች ሲኾኑ ለናንተ የገራ፣ሌሊትንና ቀንንም ለናንተ የገራላችሁ ነው። ከለመናችሁትም ሁሉ የሰጣችሁ ነው፤ የአላህንም ጸጋ ብትቆጥሩ አትዘልቁትም፤ሰው በጣም በደለኛ ከሐዲ ነው።››[ኢብራሂም፡32-34]

ከነብይነት ማረጋጋጫ ማስረጃዎች አንዱ ነው

‹‹በማይም ሕህብረተሰብ ውስጥ ያደገውና ያልተማረው ሰው ሙሐመድ፣ዘመናዊው ሳይንስ እስከ ዛሬው ዘመናችን ድረስ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግባቸውንና ቅዱስ ቁርኣን የገለጻቸውን የዩኒቨርስ ተአምራት እንዴት ማወቅ ቻለ?! ስለዚህም ይህ ንግግር የግድ የኃያሉ አላህ ቃል መሆን ይኖርበታል።››

ዲቦራ ራፖርተር

የአሜሪካ ጋዜጣ



https://www.path-2-happiness.com/am

3- ከጌታችሁ ጋር እንደምትገናኙ ታረጋግጡ ዘንድ

የሰውን ልጅ አፈጣጠር ትተን የሰማያትንና የምድርን አፈጣጠር ብናስተውል ከሞት በኋላ ዳግም መቀስቀስና ሌላ ሕይወት ስለመኖሩ ግልጽ ማስረጃ ማየት እንችላለን። የነበረውን መመለስ የሌለውን አዲስ ከመፍጠር የቀለለ አይደለምን?! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَهُوَ ٱلَّذِي يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَهُوَ أَهۡوَنُ عَلَيۡهِۚ}[الروم:٢٧]

‹‹እርሱም ያ መፍጠርን የሚጀምር፣ ከዚያም የሚመልሰው ነው፤ እርሱም (መመለሱ) በርሱ ላይ በጣም ገር ነው፤››[አል ሩም:27]

ይልቁንም ሰማያትንና ምድርን መፍጠር ሰውን ከመፍጠር በጣም የላቀ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{لَخَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ أَكۡبَرُ مِنۡ خَلۡقِ ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٥٧}[غافر: ٥٧]، (٧)

‹‹ሰማያትንና ምድርን መፍጠር፣ ሰዎችን ከመፍጠር ይልቅ ታላቅ ነው፤ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።››[አል ሙእሚን:57]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ ٱلَّذِي رَفَعَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ بِغَيۡرِ عَمَدٖ تَرَوۡنَهَاۖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ وَسَخَّرَ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ كُلّٞ يَجۡرِي لِأَجَلٖ مُّسَمّٗىۚ يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَ يُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لَعَلَّكُم بِلِقَآءِ رَبِّكُمۡ تُوقِنُونَ ٢}[الرعد: ٢].

‹‹አላህ ያ ሰማያትን የምታዩዋት አዕማድ ሳትኖር ያነሳት፣ ከዚያም በዐርሹ (ዙፋኑ) ላይ የተደላደለ፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ነው፤ ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ፤ ነገሩን ሁሉ ያስተናብራል፤ በጌታችሁ መገናኘት ታረጋግጡ ዘንድ ታምራቶችን ይዘረዝራል።››[አል ረዕድ:2]

እውነት አንድ ብቻ ነው

‹‹አንዲህ ዓይነቱን ፍጥረት እየተመለከትክ በአላህ አለማመን እንደኔ ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው . . እምነቴን የበለጠ ጠንካራ አድርጎታልና እውነታውን የሚገልጹ ቃላት እንዲኖሩ ፍላጎቴ ነው።››

ጆን ገሊን
የመጀመሪያው አሜሪካዊ የጠፈር ተጓዥ

በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ እርስዎ የት ነዎት?!

ይህ በጣም ግዙፍ ከሆኑ የጋላክሲዎች ስብስብ ያንዱ ፎቶግራፍ ነው። ከነዚህ አንዱ ወይም በአንዲት ትንሽ ነጥብ ብቻ የሚወከለው የኛ ፀሐያዊ ሥርዓት (Solar System) ያለበት የፍኖተ ሐሊብ (Milky Way) ጋላክሲ ነው። በኛ ጋላክሲ ውስጥ ከ100000000000 የሚበልጡ ፀሐዮች የሚገኙ ሲሆን፣ የኛዋ ፀሐይ ከመሬት 1300000 ጊዜ ትበልጣለች። የርስዎ ቤት 500 ካሬ ሜትር ነው ብንል መሬት ደግሞ 1020144000000 ጊዜ ከቤትዎ ትበልጣለች። የርስዎ ቤት ከርስዎ በምን ያህል እጥፍ ይበልጥ ይሆን?!



ከውቅያኖስ አንዲት ጠብታ

እስከ ዛሬ ድረስ የታወቀው ትልቁ ኮከብ VYCanis Majoris የተባለ ሲሆን ከኛ የሚርቀው በአምስት ሺ የብርሃን ዓመት ነው። መጠነቁሱ ከኛ ፀሐይ 9261000000 ጊዜ ይበልጣል። ይህም ዘጠኝ ቢሊዮን 261 ሚሊዮን ጊዜ ከፀሐይ ይገዝፋል ማለት ሲሆን ፀሐይ ደግሞ መሬትን 1300000 ጊዜ ትበልጣለች!!

ሰውን መፍጠሩና ክቡር ፍጡር ማድረጉ

ከዩኒቨርስ ግዝፈትና ከሰማያትና ከምድር ታላቅነት ጋር አላህ (ሱ.ወ.) ፍጥረተ ዓለሙን ሁሉ ለሰው ልጅ ጥቅም የተገራና የተመቻቸ እንዲሆን አድርጎታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ}[الجاثية: 13]

‹‹ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፤››[አል ጃሚያህ:13]

ይህም የሰው ልጅ የርሱ ክቡር ፍጡር በመሆኑና ከተቀሩት ፍጥረታት ሁሉ በላይ ያላቀው በመሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ كَرَّمۡنَا بَنِيٓ ءَادَمَ وَحَمَلۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَرَزَقۡنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَفَضَّلۡنَٰهُمۡ عَلَىٰ كَثِيرٖ مِّمَّنۡ خَلَقۡنَا تَفۡضِيلٗا ٧٠}[الإسراء: ٧٠].

‹‹የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፤ በየብስና በባሕርም አሳፈርናቸው፤ ከመልካሞችም (ሲሳዮች ሰጠናቸው)፤ ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።››[አል አስራእ:70]

አላህ (ሱ.ወ.) የመጀመሪያውን ሰው የአደምን አፈጣጠርና እንዴት እንደ አከበረው፣ ከዚያም በሰይጣን ጉትጎታና በጥፋቱ ከገነት ወደ መሬት እንዴት እንዳወረደው፣ በኋላም አንዴት ይቅር ብሎ ምሕረት እንዳደረገለት ተርኮልናል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ خَلَقۡنَٰكُمۡ ثُمَّ صَوَّرۡنَٰكُمۡ ثُمَّ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ لَمۡ يَكُن مِّنَ ٱلسَّٰجِدِينَ ١١ قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسۡجُدَ إِذۡ أَمَرۡتُكَۖ قَالَ أَنَا۠ خَيۡرٞ مِّنۡهُۖ خَلَقۡتَنِي مِن نَّارٖ وَخَلَقۡتَهُۥ مِن طِينٖ ١٢ قَالَ فَٱهۡبِطۡ مِنۡهَا فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا فَٱخۡرُجۡ إِنَّكَ مِنَ ٱلصَّٰغِرِينَ ١٣ قَالَ أَنظِرۡنِيٓ إِلَىٰ يَوۡمِ يُبۡعَثُونَ ١٤ قَالَ إِنَّكَ مِنَ ٱلۡمُنظَرِينَ ١٥ قَالَ فَبِمَآ أَغۡوَيۡتَنِي لَأَقۡعُدَنَّ لَهُمۡ صِرَٰطَكَ ٱلۡمُسۡتَقِيمَ ١٦ ثُمَّ لَأٓتِيَنَّهُم مِّنۢ بَيۡنِ أَيۡدِيهِمۡ وَمِنۡ خَلۡفِهِمۡ وَعَنۡ أَيۡمَٰنِهِمۡ وَعَن شَمَآئِلِهِمۡۖ وَلَا تَجِدُ أَكۡثَرَهُمۡ شَٰكِرِينَ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

﴿١٧﴾ قَالَ ٱخۡرُجۡ مِنۡهَا مَذۡءُومٗا مَّدۡحُورٗاۖ لَّمَن تَبِعَكَ مِنۡهُمۡ لَأَمۡلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿١٨﴾ وَيَٰٓـَٔادَمُ ٱسۡكُنۡ أَنتَ وَزَوۡجُكَ ٱلۡجَنَّةَ فَكُلَا مِنۡ حَيۡثُ شِئۡتُمَا وَلَا تَقۡرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٩﴾ فَوَسۡوَسَ لَهُمَا ٱلشَّيۡطَٰنُ لِيُبۡدِيَ لَهُمَا مَا وُۥرِيَ عَنۡهُمَا مِن سَوۡءَٰتِهِمَا وَقَالَ مَا نَهَىٰكُمَا رَبُّكُمَا عَنۡ هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةِ إِلَّآ أَن تَكُونَا مَلَكَيۡنِ أَوۡ تَكُونَا مِنَ ٱلۡخَٰلِدِينَ ﴿٢٠﴾ وَقَاسَمَهُمَآ إِنِّي لَكُمَا لَمِنَ ٱلنَّٰصِحِينَ ﴿٢١﴾ فَدَلَّىٰهُمَا بِغُرُورٖۚ فَلَمَّا ذَاقَا ٱلشَّجَرَةَ بَدَتۡ لَهُمَا سَوۡءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا يَخۡصِفَانِ عَلَيۡهِمَا مِن وَرَقِ ٱلۡجَنَّةِۚ وَنَادَىٰهُمَا رَبُّهُمَآ أَلَمۡ أَنۡهَكُمَا عَن تِلۡكُمَا ٱلشَّجَرَةِ وَأَقُل لَّكُمَآ إِنَّ ٱلشَّيۡطَٰنَ لَكُمَا عَدُوّٞ مُّبِينٞ ﴿٢٢﴾ قَالَا رَبَّنَا ظَلَمۡنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمۡ تَغۡفِرۡ لَنَا وَتَرۡحَمۡنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴿٢٣﴾ قَالَ ٱهۡبِطُواْ بَعۡضُكُمۡ لِبَعۡضٍ عَدُوّٞۖ وَلَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُسۡتَقَرّٞ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٖ ﴿٢٤﴾ قَالَ فِيهَا تَحۡيَوۡنَ وَفِيهَا تَمُوتُونَ وَمِنۡهَا تُخۡرَجُونَ ﴿٢٥﴾

[الأعراف: ١١- ٢٥].

‹‹በእርግጥም ፈጠርናችሁ፤ ከዚያም ቀረጽናችሁ፤ ከዚያም ለመላእክቶች ለአደም ስገዱ አልን፤ ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ሲቀር፤ ከሰጋጆቹ አልኾነም። (አላህ) ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው፤ እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ፤ ከእሳት ፈጠርከኝ፤ እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው አለ። ከርሷ (ከገነት ወይም ከሰማያት) ውረድ፤ በርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባምና፤ ወጣም፤ አንተ ከወራዶቹ ነህና አለው፤

፦ እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ አለ። አንተ ከሚቆዩት ነህ አለው።

፦ ስለ አጠመምከኝም ለነርሱ በቀጥተኛው መንገድ ላይ በእርግጥ እቀመጥባቸዋለሁ አለ። ከዚያም ከስተፊቶቻቸው፤ ከኋላቸውም፤ ከቀኞቻቸውም፤ ከግራዎቻቸውም፤ በእርግጥ እመጣባቸዋለሁ፤ አብዛኞቻቸውንም አመስጋኞች ኾነው አታገኛቸውም (አለ)።

፦ የተጠላህ ብራሪ ስትኾን ከርሷ ውጣ፤ ከነርሱ የተከተለህ ከናንተ ከመላችሁም ገሀነምን በእርግጥ እሞላታለሁ አለው። ኣደምም ሆይ! አንተም ሚስትህም በገነት ተቀመጡ፤ ከሻችሁትም ስፍራ ብሉ፤ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ (ራሳቸውን) ከሚበድሉት ትኾናላችሁና (አላቸው)። ሰይጣንም ከዕፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ለነርሱ ሊገልጥባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው፤ ጌታችሁም መልኣኮች እንዳትኾኑ ወይም ከዘላለም ነዋሪዎች እንዳትኾኑ እንጂ ከዚች ዛፍ አልከለከላችሁም አላቸው። እኔ ለናንተ በእርግጥ ከሚመክሯችሁ ነኝ ሲልም ማለላቸው። በማታለልም አዋረዳቸው፤ ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ፤ ዕፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለጠችላቸው፤ ከገነት ቅጠልም በላያቸው ላይ ይደርቱ ጀመር፤ ጌታቸውም ከዚቻችሁ ዛፍ አልከለከልኋችሁምን? ሰይጣንም ለናንተ ግልጽ ጠላት ነው አላልኋችሁምን? ሲል ጠራቸው።

፦ ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን፤ ለኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን አሉ። (አላህ) ፦ ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፤ ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ተወሰነ ድረስ

ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው

‹‹ሰዎች ሁሉ በክብርና በመብቶች ነጻና እኩል ሆነው አእምሮና ሕሊና ተሰጥተዋቸው ይፈጠራሉ፤ በመሆኑም አንዳቸው ከሌላው ጋር በወንድማዊ የአብሮነት መንፈስ መነዋነዋር ይኖርበታል።››

የሰብአዊ መብቶች ድርጅት
የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ዐዋጅ

መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ፤ አላቸው።›› [አል አዕራፍ፡11-24]

አላህ (ሱ.ወ.) ሰውን እጅግ ባማረ ቅርጽ ፈጥሮት ከመንፈሱ ነፍቶበታል፤ በዚህም የተስተካከለ ቁመና ያለው ሕያው፤ የሚሰማ የሚያይ፤ የሚናገርና የሚንቀሳቀስ ድንቅ ክቡር ፍጡር አደረገው፦

{فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحۡسَنُ ٱلۡخَٰلِقِينَ ﴿١٤﴾}[المؤمنون: ١٤]،

‹‹ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የኾነው አላህ ላቀ።›› [አል ሙእሚኑን፡12-16]

የሚያስፈልገውንም ሁሉ አስተማረው። ለሌሎች ፍጥረታት ያልተሰጡ እንደ አእምሮ፤ ዕውቀት፤ ንግግር፤ ውብ ቅርጽ፤ ያማረ ተክለ ሰውነት፤ ክቡር ቁመና፤ መካከለኛ አካል፤ የማሰብ፤ የመማርና የማገናዘብ ችሎታ . . የመሳሰሉ ተሰጥኦዎችና ባሕርያት ባለቤት አደረገው። ወደ መልካም ስነምግባራትና ውብ ጸባያትም መራው፤ ከፈጠራቸው ብዙ ፍጥረታትም አላቀው። ከነዚህ የከበሬታዎቹ መገለጫዎች መካከል የሚኪሉትን እናገኛለን ፦

- አላህ (ሱ.ወ.) ከመጀመሪያው ኣደምን የፈጠረው በእጁ ነው፤ ይህም ታላቅ ክብርና አቻ የሌለው ደረጃ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قَالَ يَٰٓإِبۡلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسۡجُدَ لِمَا خَلَقۡتُ بِيَدَيَّۖ أَسۡتَكۡبَرۡتَ أَمۡ كُنتَ مِنَ ٱلۡعَالِينَ ﴿٧٥﴾}[ص: ٧٥].

‹‹(አላህም) ኢብሊስ ሆይ! በሁለት እጆቹ ለፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮራህን? ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞቹ ነበርክ አለው።››› [ሷድ፡75]

አላህ (ሱ.ወ.) ሰውን እጅግ ባማረ አቋም ፈጥሮታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِيٓ أَحۡسَنِ تَقۡوِيمٖ ﴿٤﴾}[التين: ٧]،

‹‹ሰውንም በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው።››[አል ቲን፡4]

https://www.path-2-happiness.com/am

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ ۖ وَإِلَيْهِ الْمَصِيرُ ﴿٣﴾} [التغابن: ٣].

‹‹ቀ ረ ጻ ች ሁ ም ፤ ቅ ር ጻ ች ሁ ን ም አሳመረ፤ መመለሻችሁም ወደርሱ ነው።››[አል ተሃቡን፡3]

አላህ (ሱ.ወ.) መላእክትን በሙሉ ለሰው ልጆች አባት ለአደም እንዲሰግዱ በማዘዝ ሰውን አክብሮታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ} [الإسراء: ٦١].

‹‹ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ (አስታውስ)፤ ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፤ ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው፤ እሰግዳለሁን? አለ።››[አል እስራእ፡61]

አላህ (ሱ.ወ.) ለሰው ልጅ ማሰቢያ አእምሮ፤ ማስተዋልና ማገናዘብን፤ መስማትና መናገርን የተቀሩትንም የግንዛቤ ሕዋሳት ያደለው በመሆኑ ክቡር ፍጡር አድርጎታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَاللَّهُ أَخْرَجَكُم مِّن بُطُونِ أُمَّهَاتِكُمْ لَا تَعْلَمُونَ شَيْئًا وَجَعَلَ لَكُمُ السَّمْعَ وَالْأَبْصَارَ وَالْأَفْئِدَةَ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿٧٨﴾} [النحل: ٧٨].

‹‹አላህም ከናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ፤ ታመሰግኑም ዘንድ፤ ለናንተ መስሚያን፤ ማያዎችንም፤ ልቦችንም፤ አደረገላችሁ።››[አል ነሕል፡78]

አላህ (ሱ.ወ.) ከራሱ የሆነ መንፈስ ነፍቶበት ሰውን ክቡርና የመንፈስ ምጥቀት የተቸረው ልዩ ፍጡር አድርጎታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ فَإِذَا سَوَّيْتُهُ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُوا لَهُ سَاجِدِينَ ﴿٧٢﴾} [ص: ٧٢]،

‹‹ፍጥረቱንም ባስተካከልኩና ከመንፈሴ በነፋሁበት ጊዜ፤ ለርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ (አልኩ)።››[ሷድ፡72]

ይህ ለሰው ልጅ እጅግ የላቀ ክብር ነው።በመሆኑም ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ክቡር ስለሆነ መከበር አለበት። ከአላህ (ሱ.ወ.) መንፈስ የተነፋበትን ክቡር ፍጡር ማዋረድና መበደልም ፈጽሞ ተገቢ አይደለም።

የኛ ተልእኮ

‹‹እርሱ የሻውን ሰው ከጭጠራን አምልኮ ወደ አላህ አምልኮ፤ ከጠባቡ ዓለማዊ ሕይወት ወደ ሰፊው፤ ከሃይማኖቶች ግፍ ወደ እስላም ፍትሕ እንድናወጣ አላህ ልኮናል።››

ሩበኒ ብን ዓምር

ከአላህ መልክተኛ ﷺ ባልደረቦች አንዱ

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) መላእክትንና ጋኔን ከልክሎ ሰውን መርጦ በምድሪቱ ላይ ተጠሪው አድርጎታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً ۖ قَالُوا أَتَجْعَلُ فِيهَا مَن يُفْسِدُ فِيهَا وَيَسْفِكُ الدِّمَاءَ وَنَحْنُ نُسَبِّحُ بِحَمْدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَ ۖ قَالَ إِنِّي أَعْلَمُ مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾} [البقرة: ٣٠]،

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላእክት ፦ እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤ ባለ ጊዜ፤ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ፤ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን? አሉ፤ (አላህ) እኔ የማታውቁትን ነገር ዐውቃለሁ አላቸው።››[አል በቀራህ፡30]

ይህ ትእዛዙን የማይጥሱ፤ ዘውትር እርሱን በማወደስ፤ በማመስገን እና በማጥራት ላይ የተሰማሩት ቅን አገልጋዮቹ መላእክት እንኳን ያላገኙት ታላቅ ደረጃ ነው።

- አላህ (ሱ.ወ.) በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ በሰማያትና በምድር ያሉትን ሁሉ፤ ፀሐያትና ጨረቃዎችን፤ ከዋክብት እና ፕላኔቶችን፤ ጋላክሲዎችን እና ፀሐያዊ ጭፍራን . . ለዚህ ክቡር ፍጡር ለሰው ልጅ የተገሩለት እንዲሆኑ አድርጓል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا مِّنْهُ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿١٣﴾} [الجاثية: ١٣]

‹‹ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፤ ››[አል ጃሢያህ፡13]

አላህ (ሱ.ወ.) መላውን የሰው ዘር የፈለገውን ያህል ክብርና ደረጃ ቢኖረው እንኳ ለማንኛውም ዓይነት ፍጡር ተገዥ ከመሆን ነጻ አውጥቷል። ይህም ከሰብአዊ ፍጡራን አምልኮና ተገዥነት ወደ ጎያሉ አላህ አምልኮና ተገዥነት የሚያሸጋግረው በመሆኑ ለሰው ልጅ ከምንም በላይ የሆነ የላቀ የነጻነት ደረጃ ነው። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) በራሱና በአገልጋይ ባሮቹ መካከል የሚገባ አማላጅም ሆነ አገናኝን የማይቀበለው። ይሁን እንጂ አንዳንዳንድ ወገኖች በሰው ልጅና በፈጣሪ ጌታው መካከል የአምላክነት ባህርያትና መብት የሰጧቸውን አማላጅ አገናኞችን ከራሳቸው ፈጥረው አቅርበዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ያሉትን አማላጆች ውድቅ በማድረግ የሰውን ልጅ አክብሮታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{اتَّخَذُوا أَحْبَارَهُمْ وَرُهْبَانَهُمْ أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ وَالْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا إِلَٰهًا وَاحِدًا ۖ لَّا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۚ سُبْحَانَهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٣١﴾} [التوبة: ٣١].

‹‹ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊግዘዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ፤ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፤ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።››[አል ተውቡህ፡31]\

https://www.path-2-happiness.com/am

የሰውን ልጅ በቀዲእና በቀደር በማመንና ቁሳዊ ጥረትን ከውጤት ጋር በማያያዝ አማካይነት ከመጻኢው ጊዜ ስጋት፣ከጭንቀት፣ተስፋ ከመቁረጥና ከማዘን አላህ (ሱ.ወ) ነጻ አውጥቶታል። በቀዲእና በቀደር ማመን ማለትም አላህ (ሱ.ወ.) ሁሉንም ነገር ከመከሰቱ በፊት ወስኖ እርሱ ዘንድ የመዘገበው መሆኑንና ከርሱ ውሳኔና መሻት ውጭ የሚሆን ምንም ነገር አለመኖሩን ማመን፣አማኙን ሰው በሰላምና በእርጋታ፣በራስ በመተማመንና በከበሬታ፣በተገቢው መንገድ ሳቢያን ከውጤት በማገናኘት ማድረግ የሚገባውን ሁሉ እስከፈጸመ ድረስም የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) የሻውና የወሰነው ነውና ባለፈውና ባመለጠው



አገናኝ አማላጅ የለም

‹‹አንድ ዐብይ ጉዳይ አለ፣እሱም በፈጣሪ ጌታና በአገልጋይ ባሪያው መካከል አገናኝ አማላጅ አለመኖሩ ነው። ይህ አርቆ አስተዋዮች የደረሱበት እውነታ ነው።››

ኤይቱን ዴኔህ
ፈረንሳዊ ሠዓሊና አሳቢ

ነገር ባለ መቆጨትና ባለ ማዘን ሁኔታ ውስጥ እንዲኖር ያደርገዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَآ أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فِيٓ أَنفُسِكُمۡ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مِّن قَبۡلِ أَن نَّبۡرَأَهَآۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ٢٢}[الحديد: ٢٢]،

‹‹በምድርም፣በነፍሶቻችሁም፣መከራ (ማንንም) አትነካም፣ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትሆን እንጅ፣ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።››[አል ሐዲድ:22]

ይህ እምነት ባለቤቱን ሚዘናዊ አእምሮ ኖሮት በእውነተኛ የስነልቦና መረጋጋትና በከፍተኛ የመተማመን ሁኔታ ውስጥ አንዲኖር ያደርገዋል። ችግርና መከራ ሚዛን አሳጥተውት ተጽእኖ የማያሳድሩበት፣ደስታና ምቾትም ትእቢትና መንበጣረርን የማያስከትሉበት ሚዛኑን የጠበቀ ሰብእና እንዲላበስ ያስችለዋል።

አላህ (ሱ.ወ.) ለሰው ልጅ አእምሮና ለአስተሳሰቡ ከፍተኛ ዋጋ ሰጥቷል፣እንዲያስተውልና እንዲያስተነትንም አዞታል። የሰማያትንና የምድርንም አፈጣጠር ማስተንተንን፣ምክንያታዊ አስረጅና ትንተና ማቅረብንም ግዴታ አድርጓል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلِ ٱنظُرُواْ مَاذَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَا تُغۡنِي ٱلۡأٓيَٰتُ وَٱلنُّذُرُ عَن قَوۡمٖ لَّا يُؤۡمِنُونَ ١٠١}[يونس: ١٠١]،

‹‹ፉ በሰማያትና በምድር ያለውን (ታምር) ተመልከቱ፣በላቸው፣ታምራቶችና አስፈራሪዎችም፣ለማያምኑ ሕዝቦች አይጠቅሙም።›› [ዩኑስ:101]

አእምሮ እንዲከበርና ትኩረት እንዲሰጠው፣እንዲሠራና እንዲያስተውል እንዲደረግ፣በጭፍን ተከታይነትና ወገንተኝነት አማካይነት ከሥራ ውጭ እንዳይደረግ አሏል። በሰው ልጅ ላይ የተጣለው ኃላፊነትና ግዴታ ከአእምሮ ጋር የተያያዘና ከርሱ ውጭ የማይሆን ከማድረጉም በላይ ለርሱ መኖር ማስረጃና ለአንድነቱም አመላካች አድርጎታል። የአመለካከት ልዩነት ሲኖርም በአእምሯዊ የማስረጃ አቀራረብ ስልት መዳኘትንም አሏል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١١١}[البقرة: ١١١]،

‹‹ገነትንም አይሁድን፣ወይም ክርስቲያኖችን የኾነ እንጂ አይገባትም አሉ፣ይህቺ (ከንቱ) ምኞታቸው ናት፣እውነተኞች እንደ ኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው።››[አል በቀራህ:111]

አእምሮን ከአፈተረት፣ከአባይ ጠንቋይ ማጭበርበር፣ቢጋኔንና በመናፍስት ከመታገዝና ከመሳሰሉት ነገሮችም ነጻ እንዲሆን አድርጎታል።

እያንዳንዱ ሰው በሠራውና በፈጸመው ነገር በግሉ ኃለፊና ተጠያቂ መሆኑን አረጋግጦ፣አንዱ በፈጸመው ነገር ሌላው ተጠያቂ አለመሆኑን ገልጾታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٞ وِزۡرَ أُخۡرَىٰ} [فاطر: ١٨]،

‹‹ነጢአትን ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላዋን ሸክም አትሸከምም፣››[ፋጢር:18]

ቁርኣን በነዚህ የሰው ልጅ የክቡርነት መገለጫዎች፣የውርስ ኃጢአት ጽንሰ ሐሳብን ውድቅ አድርጎ በማስወገድ የሰውን ዘር ከሸክሙ ነጻ አድርጓል።

https://www.path-2-happiness.com/am

ሴትን ከወንድ ጋር እኩል ማድረግ፦

ለሰው ልጅ የተሰጠው ከበሬታ በአንድ ጾታ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ከበሬታው በመሰረቱ ልክ እንደ ወንዱ ሴቷንም ያጠቃለለ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَهُنَّ مِثْلُ ٱلَّذِى عَلَيْهِنَّ بِٱلْمَعْرُوفِ} [البقرة: ٢٢٨]،

‹‹ለነርሱም (ለሴቶች) የዚያ በነርሱ ላይ ያለባቸው (ግዳጅ) ብጤ በመልካም አኑዋኑዋር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው፤›› [አል በቀራህ:228]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلْمُؤْمِنُونَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتُ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَآءُ بَعْضٍ} [التوبة: ٧١]،

‹‹ምእመናንና ምእመናትም ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፤›› [አል ተውባህ:71]

በወዲያኛው ዓለም ሽልማትና ምንዳ ሴት ልጅ ፈጽሞ ከወንዱ አትለይም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَٱسْتَجَابَ لَهُمْ رَبُّهُمْ أَنِّى لَآ أُضِيعُ عَمَلَ عَٰمِلٍ مِّنكُم مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ بَعْضُكُم مِّنۢ بَعْضٍ} [آل عمران:١٩٥]،

‹‹ጌታቸውም እኔ ከናንተ፤ከወንድ ወይም ከሴት፤የሠሪን ሥራ አላጠፋም፤ከፊላችሁ ከከፊሉ ነው፤በማለት ለነርሱ ልመናቸውን ተቀበለ፤›› [አል ዒምራን:195]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يَعْمَلْ مِنَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُوْلَٰٓئِكَ يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ وَلَا يُظْلَمُونَ نَقِيرًا ﴿١٢٤﴾} [النساء: ١٢٤].

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፤እርሱ አማኝ ኾኖ ከበጎ ሥራዎች አንዳችን የሚሠራም ሰው፤እነዚያ ገነትን ይገባሉ፤በተምር ፍሬ ላይ ያለችን ነጥብ ያክል

እኩል መብት

‹‹የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 26 ቀን 1964 ዓመተ ልደት ካስተላለፈው ውሳኔ በፊት የሴትና የወንድ ተማሪዎችን መብት (በክበባትና በተማሪዎች ማህበራት ውስጥ) እኩል አድርጎ አያውቅም።››

እውነተኛው ተአምርa

‹‹የቁርአንን መሰረታዊ መርሆዎች ከርሱ ከቀደሙት ሕብረተሰቦች ሁሉ ጋር በተለይም ሴት ልጅ በቋሚነት መልኩ ጎደሎ ተደርጋ ትወሰድ ከነበረበት ከአቱና እና ከሮማ ሁኔታ ጋር ብናነጻጽር፤ምንም ክርክር የሌለበት እድገት ያስመዘገቡ ናቸው።››

ሮገር ጋሩዲ
ፈረንሳዊ ፈላስፋ

እንኳ አይበደሉም።››[አል ኒሳእ:124]

አላህ (ሱ.ወ.) ልክ እንደ ወንዱ ሁሉ ሴቷም ሙሉ ኃላፊነትንና ግዴታን ለመሸከም ብቁ፤ በሽልማትም ሆነ በቅጣትም ከወንዱ ጋር እኩል ሲያደርጋት ሴትን ክቡር ፍጡር አድርጓታል። ሌላው ቀርቶ ለሰው ልጅ የተላለፈው የመጀመሪያው መለኮታዊ ትእዛዝ ለወንዱና ለሴቷም ለመጀመሪያው ሰው ለኣደምና ለሐዋ በአንድ ላይ የተላለፈ ነበር። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقُلْنَا يَٰٓـَٔادَمُ ٱسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ ٱلْجَنَّةَ وَكُلَا مِنْهَا رَغَدًا حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٣٥﴾} [البقرة : ٣٥]،

‹ኣደም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ከበደለኞች ትኾናላችሁና አልንም።››[አል በቀራህ:35]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) የኣደምን ከገነት መውጣትና የዝርዮቹን መከራ፤በአንዳንድ ሃይማኖቶች ውስጥ እንደሚነገረው ዓይነት ተጠያቂነቱን በሔዋን ላይ አላደረገም። ይልቁንም አደምን ነው የመጀመሪያው ተጠያቂ አድርጎ የጠቀሰው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ عَهِدْنَآ إِلَىٰٓ ءَادَمَ مِن قَبْلُ فَنَسِىَ وَلَمْ نَجِدْ لَهُۥ عَزْمًا ﴿١١٥﴾} [طه: ١١٥]، {وَعَصَىٰٓ ءَادَمُ رَبَّهُۥ فَغَوَىٰ ﴿١٢١﴾ ثُمَّ ٱجْتَبَٰهُ رَبُّهُۥ فَتَابَ عَلَيْهِ وَهَدَىٰ ﴿١٢٢﴾} [طه: ١٢١ - ١٢٢].

‹‹ወደ ኣደምም ከዚህ በፊት ኪዳንን በእርግጥ አወረድን፤ረሳም፤ለርሱም ቆራጥነትን አላገኘንለትም።››[ጣሃ:115]

‹‹ከርሷም፤በልሉ፤ለነርሱም ሐፍረተ ገላቸው ተገለጸች፤ከገነትም ቅጠል በላያቸው ላይ ይለጥፉ ጀመር፤ኣደምም የጌታውን ትእዛዝ፤(ረስቶ) ጣሰ፤(ከፈለገው መዘውተር) ተሳሳተም። ከዚያም ጌታው መረጠው፤ከርሱም ጸጸቱን ተቀበለው፤መራውም።››[ጣሃ:121-122]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሴት በሰው ሰራሽ ሕጎች ውስጥ

‹‹ሮማ ውስጥ ትልቅ ጉባኤ ተደርጎ በሴቶች ጉዳይ ላይ ተነጋገረ። ሴት ነፍስ የሌላት ፍጡር ናት፣በዚህ ጉድለት ምክንያትም መንግሥቱ ስማያትን አትወርስም፣እርኩስ ስለሆነች ሥጋ መብላትም ሆነ መሳቅና መናገርም የለባትም፤ሙሉ ጌዜዋንም በጸሎት፣በአምልኮና በአገልግሎት ማሳለፍ ይኖርባታል ብሎ ወሰነ። ከዚህ ሁሉ ሊከለክሏት በማሰብም በአፉዋ ላይ የብረት ቁልፍ ዘለበት አደረጉ። የከፍተኛውና የዝቅተኛውም ቤተሰብ ሴት መንገድ ላይ ትጓዝ የነበረውና ወጥታ የምትገባው አፉዋ እንደተቆለፈ ሆኖ ነበር። ይህም ሴት ልጅ የወንዶች ልብ ለማበላሸት ሰይጣን የሚገለገልባት የማሳሳቻ መሣሪያ ተደርጋ ከመወሰዷ አንጻር ይፈጸምባት ከነበረው አካላዊ ቅጣቶች በተጨማሪ ነው።››

ሴት እነርሱ ዘንድ . .

‹‹በጥንታዊ የሕንድ ሕግጋት ውስጥ ፦ ተላላፊ በሽታ፣ሞት፣ ኅሀነም፣መርዝ፣እባቦችና እሳት ከሴት የተሻሉ ናቸው። በሕይወት የመኖር መብቷ ባለ ንብረት ጌታዋ ከሆነው ባሏ መሞት ጋር ያከትማል፤አስከሬኑ መቃጠሉን ካየች ራሷን ወደ እሳቱ ትወረውራለች፤ባታደርግ ዘላለማዊ እርግማን ይወርድባታል።››

እነሆም ሴቶችና ወንዶች በሰብአዊነት በዚህ መልኩ እኩል ተደርገዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ١٣}[الحجرات: ١٣].

በዚህ መልኩም ወንዶችና ሴቶች በሚከተሉት ጉዳዮች እኩልና ተጋሪዎች ናቸው ፦

በግላዊ ቁሳዊ መብቶች የሕግ ኃላፊነት፦ የሴት ልጅ የሕግ ሰውነት የታፈረና የተከበረ ነው። ግዴታን በመወጣትና በመታዘዝ ብቁነት ላይ አላህ (ሱ.ወ.) ከወንዱ ጋር እኩል አድርጓት በመብቷ የመጠቀምን፣ንብረት የመያዝ፣ የማስተዳደርና ውል የመዋዋል፣መሸጥና መግዛትን የመሳሰሉትን ሁሉ አረጋግጦላታል። እነዚህ የሲቪል መብቶቿ በአፈጻጸም በወንዱም ላይ ከሚጣል ገደብ ውጭ ያለ ምንም ገደብ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لِّلرِّجَالِ نَصِيبٞ مِّمَّا ٱكۡتَسَبُواْۖ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٞ مِّمَّا ٱكۡتَسَبۡنَۚ}[النساء: ٣٢]፣

‹‹አላህም ከፊላችሁን በከፊሉ ላይ በርሱ ያበለጠበትን ጸጋ አትመኙ። ለወንዶች ከሠሩት ሥራ ዕድል አላቸው፤ለሴቶችም ከሠሩት ሥራ ዕድል አላቸው። አላህንም ከችሮታው ለምኑት፤አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነውና። ››[አል ኒሳእ:32]

የውርስ መብቷን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لِّلرِّجَالِ نَصِيبٞ مِّمَّا تَرَكَ ٱلۡوَٰلِدَانِ وَٱلۡأَقۡرَبُونَ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٞ مِّمَّا تَرَكَ ٱلۡوَٰلِدَانِ وَٱلۡأَقۡرَبُونَ مِمَّا قَلَّ مِنۡهُ أَوۡ كَثُرَۚ نَصِيبٗا مَّفۡرُوضٗا ٧}[النساء: ٧]፣

‹‹ለወንዶች፣ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት (ንብረት) ፈንታ አላቸው። ለሴቶችም፣ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ከርሱ ካነሰው ወይም ከበዛው፣ፈንታ አላቸው። የተወሰነ ድርሻ (ተደርጓል)።››[አል ኒሳእ:7]

በሕግ ፊትም በደንም ሆነ በክፉ ከወንድ ጋር ሙሉ በሙሉ እኩል ተደርጋለች። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلسَّارِقُ وَٱلسَّارِقَةُ فَٱقۡطَعُوٓاْ أَيۡدِيَهُمَا جَزَآءَۢ بِمَا كَسَبَا نَكَٰلٗا مِّنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ٣٨}[المائدة: ٣٨].

በወዲያኛው ሕይወት ሽልማትና ቅጣትም ከወንዱ ጋር እኩል ነች። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَنۡ عَمِلَ صَٰلِحٗا مِّن ذَكَرٍ أَوۡ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَلَنُحۡيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةٗ طَيِّبَةٗۖ وَلَنَجۡزِيَنَّهُمۡ أَجۡرَهُم بِأَحۡسَنِ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٩٧}[النحل: ٩٧].

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።››[አል ነሕል:97]

በመረዳዳትና በመተጋገዝም እኩል ናቸው።አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلۡمُؤۡمِنُونَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلِيَآءُ بَعۡضٖۚ يَأۡمُرُونَ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَيُطِيعُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓۚ أُوْلَٰٓئِكَ سَيَرۡحَمُهُمُ ٱللَّهُۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ٧١}[التوبة: ٧٢].

‹‹ምእመናንና ምእመናትም፣ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፤በደግ ነገር ያዛሉ፤ክፉም ይከለክላሉ፤ሶላትንም ይሰግዳሉ፤ዘካንም ይሰጣሉ፤አላህንና መልክተኛውንም



እንዴት ያለ ግፍ ነው?!

‹‹ሴት ከወንድ አኳያ እንደ ባሪያና እንደ ጌታ፣እንደ አእምሮ ሥራና የጉልበት ሥራ፣እንደ በርበርና እንደ ግሪካዊ ናት፤ሴት ልጅ ጎደሎ ሰው ስትሆን ከእድገት መስላል የታችኛው ደረጃ ላይ ቆማ እንድትቀር ተደርጋለች።››

አርስቶትል

የግሪክ ፈላስፋ

ፈረንሳይቷ ሴት

‹‹በ586 ዓመተ ልደት በፈረንሳይ አንድ ክፍለ አገር ውስጥ ሴት ሰው ተደርጋ ትቆጠራለች ወይስ ሰው አይደለችም? በሚለው ጉዳይ ላይ ለመወሰን ጉባኤ ተደርጓል። በጉባኤው መጨረሻ ተሰብሳቢዎች የደረሱበት ውሳኔ፣ሴት ሰው ነች፣የተፈጠረችው ግን ወንድን ለማገልገል ነው የሚል ነበር። የፈረንሳይ ሴቶችን በንብረታቸው ላይ የማዘዝ መብት የሚገድቡ ሕጎች ተሽረው ለመጀመሪያ ጊዜ ፈረንሳይቱ ሴት መብቷ የተከበረላትና በስሟ ተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳብ እንድትከፍት የተፈቀደላት የካቲት 1938 ዓመተ ልደት በወጣ ሕግ ነበር።››



https://www.path-2-happiness.com/am

መብቷ የተጨፈለቀው ሴት

‹‹አውቅና እመረምር ዘንድ፣ኃጢአትም ስንፍና፣ስንፍናም እብደት እንደ ሆነች አውቅ ዘንድ እኔ በልቤ ዞርሁ። እኔም ከሞት ይልቅ የመረረ ነገር መርምሬ አገኘሁ፣እርስዋም ልቡዋ ወጥመድና መርበብ የሆነ፣እጆቿም እግር ብረት የሆኑ ሴት ናት፣›› መጽሐፈ መክብብ 7፡ 25-26

መጽሐፍ ቅዱስ

የተሟላ እኩልነት

‹‹ሴት ልጅ በእስላም ጥላ ስር ነጻነቷን አስመልሳለች፣የላቀ ደረጃ ለመያዝም በቅታለች። እስላም ሴቶችን ከወንዶች ጋር ሙሉ በሙሉ እኩል የሆኑ አንዱ ሌላውን የሚያሟላ ወንድማማችና እህትማማች አድርጎ ነው የሚወስደው። ሴት እንድትማር፣ትምህርትና ዕውቀትን እንድትሰነቅ ጥሪ አድርጓል። ንብረት የመያዝ መብትና በንብረቷ ላይ የማዘዝ ነጻነትም ሰጥቷታል። የጋብቻ ውል የመፈጸም መብትም አጎናጽፏታል። የሀሳብና የንግግር መብትም አቀዳጅቷታል።››

ሙና ማክሎስኪ

ጆርመናዊት ዲፕሎማት

ይታዘዛሉ፣እነዚያን አላህ በእርግጥ ያዘንላቸዋል፣አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና።››[አል ተውባህ፡72]

ለሴቶች እገዛትና ርህራሄን ማሳየት የታዘዘ ሲሆን በጦርነት ላይ ሴቶችን መግደል አላህ እርም አድርጎ ከልክሏል። በወር አበባዋ ሰሞን አብሯት መሆንንና አብሮ መብላትም ታሟል። አይሁዶች ይህን ሁሉ በመከልከል በወር አበባዋ ጊዜ በአካል ይርቋታል፣ጊዜው እስኪያልፍ ድረስም አብሯት መብላትን ይከለክላሉ። የሴት ልጅ ከአላህ መልክተኛም ﷺ ግሩም የሆነ ከበሬታ ተችሯታል። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በላጫችሁ ለቤተሰቡ ከሌላው ይበልጥ ጥሩ የሆነ ሰው ነው፣እኔ ከሁላችሁም ይበልጥ ለቤተሰቤ ጥሩ ነኝ።››[በትርምዚ የተዘገበ]

በዘመናቸው አንዲት ሴት በባሏ እንደ ተመታች ሲሰሙ ተቆጥተው እንዲህ ብለው ነበር ፦ ‹‹አንዳችሁ ባለቤቱን እንደ ባሪያ ይመታትና ከዚያ በቀኑ መጨረሻ ላይ ያቅፋታል!››[በቡኻሪ የተዘገበ]

ሴቶች ተሰብስበው ባሎቻቸውን ለመክሰስ ወደ አላህ መልክተኛ r ሲመጡ እንዲህ ነብዩ ብለዋል፦ ‹‹ባሎቻቸውን የሚከሱ ብዙ ሴቶች ወደ ሙሐመድ ቤተሰብ መጥተዋል፣እነዚያ (ሚስቶቻቸውን የሚጎዱ ወንዶች) ምርጦቻችሁ አይደሉም።›› [በአቡ ዳውድ የተዘገበ]

ሴት እንደ እናት ወንድ ያላገኘውን ደረጃም አግኝታለች። አላህ (ሱ.ወ.) ከአባት በበለጠ ለእናት ደግ መሆንን አሟል። አንድ ሰው ወደ ነብዩ r መጥቶ ፦ ‹‹የአላህ መልክተኛ ሆይ! ለኔ መልካም አያያዝና ለደግነቴ ከሁሉም ይበልጥ ባለመብት የሆነው ማነው? ሲላቸው ፦ እናትህ ናት አሉት፣ከዚያስ? አላቸው፣እናትህ ናት፣አሉት፣ከዚያስ? አላቸው፣እናትህ ናት አሉት፣ከዚያስ? አላቸው፣አባትህ ነው አሉት።››[በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]

ለሴት ልጅ አስተዳደግም የሚሰተው ትኩረት ለወንዶች ልጆች አስተዳደግ ከሚሰጠው ትኩረት የበለጠ አላህ ዘንድ ምንዳ እንዳለው ሲገልጹም ነብዩ r እንዲህ ብለዋል ፦ ‹‹እነዚህ ሴት ልጆች ተሰጥተውት በነሱ የተፈተነና በጥሩ አያያዝ ደግ ለሆነላቸው ሰው፣ከገሀነም እሳት መከላከያ ይሆኑለታል።››[በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]

በተጨማሪም ነብዩ r እንዲህ ብለዋል ፦ ‹‹አላህ ሆይ! የነዚህን የሁለቱን ደካሞች የሙት ልጅንና የሴትን መብት የጣሰውን ሰው ኃጢአተኛ አድርጌያለሁ።››[በነሳኢ የተዘገበ]

ጨቋኝ ሰው ሠራሽ ሕግ

‹‹ንጉሥ ሄንሪ ስምንተኛ ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነቡ የሚከለክል ሕግ አውጥቷል። በ1850 አካባቢ ሴቶች በአጠቃላዩ የእንግሊዝ ሕግ መሰረት ዜጎች ተደርገው አይቆጠሩም ነበር። ግለሰባዊ መብቶችም አልነበሯቸውም፣ሌላው ቀርቶ በገዛ ልብሳቸው ላይ እንኳ የባለቤትነት መብት አልነበራቸውም። በግንባራቸው ላብ ባፈሩት ሀብት ላይም መብት አልተሰጣቸውም ነበር።››

ንጉሥ ሄንሪ ስምንተኛ

የሰው ልጅ መፈጠር ዓላማውና ምስጢሩ

ዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ሁሉ ለርሱ የተገራለትንና ከተቀሩት ፍጥረታት ሁሉ ክቡር የሆነው ይህን የሰው ልጅ፤አላህ (ሱ.ወ.) የፈጠረው ለታላቅ ጥበብና ለክቡር ዓላማ ነው፤እርሱ ከስንቱና ውድቅ ነገር ሁሉ የጠራ ጌታ ነውና። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٩١﴾} [آل عمران: ١٩٠- ١٩١]،

‹‹ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር፤ሌሊትና ቀንም በመተካካት፤ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው፤ ተቀምጠውም፤በጎኖቻቸው ተጋድመውም፤አላህን የሚያወሱ፤በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ፦ ጌታችን ሆይ! ይሽን በስንቱ አልፈጠርከውም፤ጥራት ይገባህ፤ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን፤የሚሉ ናቸው።››[አል ዒምራን፡190-191]

አላህ (ሱ.ወ) የክሓዲዎችን ክፉ ጥርጣሬ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا خَلَقْنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا بَٰطِلًا ۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ۚ فَوَيْلٌ لِّلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنَ ٱلنَّارِ ﴿٢٧﴾}[ص: ٢٧]

‹‹ሰማይንና ምድርን፤በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ ለስንቱ አልፈጠርንም፤ይህ የነዚያ የካዱት ሰዎች ጥርጣሬ ነው፤ለነዚያም ለካዱት ሰዎች ከእሳት ወዮላቸው!››[ሷድ፡27]

አላህ (ሱ.ወ) ሰውን እንደ ተቀሩት እንስሳት ሁሉ ለምግብና ለወሲብ ብቻ አልፈጠረውም። ክቡር ፍጡር አድርጎት ከፈጠራቸው ከብዙዎቹ ፍጡራን ያላቀው ቢሆንም ግን ብዙ ሰዎች ክህደትን መርጠዋል፤የተፈጠሩበትን ዓላማና ጥበቡን ችል ብለው ወይም አስተባብለው ዋነኛ ተልእኮአቸውን መብላት፤መጠጣትና መደሰት ብቻ በማድረጋቸው ሕይወታቸውን ወደ እንስሳት ሕይወት ተርታ እንዲዘቅጥ ብቻ ሳይሆን ከዚያም የከፋ እንዲሆን አድርገዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ يَتَمَتَّعُونَ وَيَأْكُلُونَ كَمَا تَأْكُلُ ٱلْأَنْعَٰمُ وَٱلنَّارُ مَثْوًى لَّهُمْ ﴿١٢﴾} [محمد: ١٢]،

‹‹አላህ እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሠሩትን፤ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች ያገባቸዋል፤እነዚያም የካዱት፤(በቅርቢቱ ዓለም) ይጣቀማሉ፤እንስሳዎች እንደሚበሉ ይበላሉ፤እሳትም ለነርሱ መኖሪያቸው ናት።››[መሐመድ፡12]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{ذَرْهُمْ يَأْكُلُوا۟ وَيَتَمَتَّعُوا۟ وَيُلْهِهِمُ ٱلْأَمَلُ ۖ فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ ﴿٣﴾}[الحجر: ٣]،

ወደ አላህ

‹‹ሃይማኖትና የተፈጥሮ ሳይንስ ጥርጣሬን፤ማስተባበልንና አፈተረትን በጋራ ሆነው በአንድ ዐውደ ውጊያ እየተዋጉ ነው። በዚህ ጦርነት ላይ የጋራ ጨኽት የነበረውና ለዘላለሙም የሚሆነው ‹ወደ አላህ› የሚለው ነው።››

ማርክስ ብላንክ

የይዘት (quantity/volume) ንድፈ ሐሳብ ቀማሪ

ቁልጭ ያሉ ማስረጃዎች

‹‹ፈጣሪና የበላይ ተቆጣጣሪ የሆነ ኃይል ሳይኖር የሕይወትን መጀመርም ሆነ መቀጠል ማሰብ ለሰው ልጅ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ፈላስፎች ስለሕይወት ባደረጓቸው ፍልስፍናዊ ጥናቶቻቸው ውስጥ በዩኒቨርስ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ቁልጭ ያሉ ማስረጃዎች ችላ ብለዋል የሚል እምነት አለኝ።››

ማጂንስ ማክሊያስ

የእንግሊዝ ሳይንስ ማህበር አባል

https://www.path-2-happiness.com/am

{تَبَـٰرَكَ ٱلَّذِى بِيَدِهِ ٱلْمُلْـكُ وَهُـوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيـرٌ ۝١ ٱلَّذِى خَلَـقَ ٱلْمَـوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُـمْ أَحْسَنُ عَمَـلًا ۚ وَهُـوَ ٱلْعَزِيـزُ ٱلْغَفُـورُ ۝٢} [الملك: ١-٢]،

‹‹ያ ንግሥና በእጁ የኾነው አምላክ ችሮታው በዛ ፤ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መኾኑን ሊሞክራችሁ ፤ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው ፤ እርሱም አሸናፊው መሓሪው ነው።››[አል ሙልክ፡1-2]

አርቀው በሚያስወተውሉ ሰዎች ዘንድ እንደሚታወቀው ሁሉ አንድን ነገር የሠራው ከሌላው ይበልጥ የሠራበትን ዓለማ ያውቃል።አላህም (ሱ.ወ.) ሰውን የፈጠረበትን ጥበብና ምስጢሩን ከማንም በላይ ያውቃል። እዝህ ላይ መግዛት ወይም ማምለክ የሚለው በመጸለይና በመጾም ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርሱን በመላ ማልማትንና ለሰው ልጅ ጥቅም መግራትን የሚያካትት ስፋትና ጥልቀት ያለው ትርጉሜ አለው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ وَٱسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا فَٱسْتَغْفِرُوهُ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِ} [هود: ٦١]،

‹‹እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ ፤ በውስጧ እንድታለሚትም አደረጋችሁ ፤ ምሕረቱንም ለምኑት ፤ ከዚያም ወደርሱ ተመለሱ ፤ ጌታዬ ቅርብ (ለለመነው) ተቀባይ ነውና አላቸው። ››[ሁድ፡61]

‹‹ተዋቸው ፤ ይብሉ ፤ ይጠቀሙም ፤ ተስፋም ያዘናጋቸው ፤ በእርግጥም (መጥፎ ፍጻሜያቸውን) ያውቃሉ።››[አል ሒጅር፡3]

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ ءَاذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَآ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ كَٱلْأَنْعَٰمِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْغَٰفِلُونَ ۝١٧٩} [الأعراف: ١٧٩]،

‹‹ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን ለገሀነም በእርግጥ ፈጠርን ፤ ለነርሱ በርሳቸው የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው ፤ ለነሱም በሳቸው የማያዩባቸው ዓይኖች አሉዋቸው ፤ ለነሱም በሳቸው የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሉዋቸው ፤ እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው ፤ ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው ፤ እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ናቸው።››[አል አዕራፍ፡179]

ሰዎች ሁሉ እያንዳንዱ የአካላቸው ክፍል ራሱን ለቻለ ጥበብና ምሥጢር እንደተፈጠረ በቁርጠኝነት ያረጋግጣሉ። ዓይን የተፈጠረው ለማየት ፤ ጆሮ ለመስማት ወዘተ. መሆኑን ያውቃሉ። እናም አካላቱ የተፈጠሩት ለጥበባዊ ዓላማ ሆነው እርሱ ራሱ ሰው ግን ለከንቱ የተፈጠረ እንዴት ሊሆን ይችላል?! ወይም ፈጥሮ ያስገኘው ጌታ የፈጠርከህ ለታላቅ ዓለማና ጥበብ ነው ሲለው እምቢ ማለቱ እንዴት ሊታሰብ ይችላል?!

ታድያ አላህ (ሱ.ወ.) የፈጠረን ለምን ዓለማና ለምንስ ጥበብ ይሆን? ክቡር ፍጠራን ያደረገንና ነገሮችን ሁሉ ለኛ የተገሩ ያደረገውስ ለምን ይሆን? አላህ (ሱ.ወ) ራሱ መልሱን ነግሮናል። እንዲህ በማለት፦

{وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ۝٥٦} [الذاريات: 56].

‹‹ጋኔንና ሰውንም ፤ ሊገዝዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።››[አል ዛሪያት፡56]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

አምልኮት ወይም ዕባዳ መላውን የሰው ልጅ ሕይወት የሚያካልል ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢ لَا شَرِيكَ لَهُۥۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرۡتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ١٦٣}[الأنعام: 162- 163].

‹‹ስግደቴ መገዛቴም፣ሕይወቴም፣ሞቴም፣ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል። ለርሱ ተጋሪ የለውም፤በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፤እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ (በል)።››[አል አንዓም፡162-163]

የአምልኮተ አላህ (ዕባዳ) አጠቃላይ ግንዛቤ

ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አንዳችሁ ችግኝ በእጁ እንደያዘ የትንሣኤ ቀን ቢደርስ ይትከለው (መትከሉን አይተወው)።›› [በአሕመድ የተዘገበ]

የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንዳችን የራሱን ሥጋዊ ፍላጎት አርክቶ በዚያ ምንዳ ያገኛልን?! ሲሏቸው፦ ፍላጎቱን በተከለከለ (ሐራም) መንገድ አርክቶ ቢሆን ኃጢአት ይሆንበት የለምን? በተመሳሳይ መልኩም በተፈቀደ (ሐላል) በመፈጸሙ ምንዳ ያገኝበታል።›› [በሙስሊም የተዘገበ]

ነብያዊ ሐዲስ

ሰው ሆይ! ከዚህ በኋላስ . .

ሰው ሆይ! ዩኒቨርሱ በመላ ለአንተ አገልግሎት የተገራልህ ከሆነ፣ተአምራቱና ምልክቶቹ ግልጽ ሆነው ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና አላህ ተጋሪ የሌለው አንድዬ አምላክ መሆኑን ለመመስከር ከፊትህ ከቆሙ፣ከሞትክ በኋላ አንተን ዳግም መቀስቀስና ሕያው ማድረግ ለአላህ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠር የቀለለ መሆኑን ካወቅህ፣አላህ (ሱ.ወ.) በድንቅ አቋምና በአማረ ቅርጽ የፈጠረህ፣ክቡር ፍጡር ያደረገህ፣ዩኒቨርስን ለአንተ የገራልህ መሆኑንም ከተገነዘብክ ዘንዳ በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ?! አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ٦ ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ٧ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ٨}[الانفطار: ٦-٨]،

‹‹አንተ ሰው ሆይ፣በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ? በዚያ በፈጠረህ፣አካለ መሉም ባደረገህ፣ባስተካከለህም። በማንኛውም በሻው ቅርጽ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)።››[አል እንፍጣር፡8]

በመጨረሻም አንተ ከጌታህ ጋር ትገናኛለህና። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦ فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ٧ فَسَوۡفَ يُحَاسَبُ حِسَابٗا يَسِيرٗا ٨ وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورٗا ٩ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهۡرِهِۦ ١٠ فَسَوۡفَ يَدۡعُواْ ثُبُورٗا ١١ وَيَصۡلَىٰ سَعِيرًا ١٢}[الانشقاق: ٦-١٢]،

‹‹አንተ ሰው ሆይ! አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ፤ተገናኚውም ነህ። መጽሐፉን በቀኙ የተሰጠ ሰውማ፣በእርግጥ ቀላልን ምርመራ ይመረመራል፤ወደ ቤተሰቦቹም ተደሳች ኾኖ ይመለሳል። መጽሐፉን በጀርባው ኋላ የተሰጠ ሰውማ፣(ዋ ጥፋቱ በማለት) ጥፋትን በእርግጥ ይጠራል። የተጋጋመች እሳትንም ይገባል።››[አል እንሽቃቅ፡6-12]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ለተፈጠርክበት ታላቅ ዓለማና ጥበብ በመኖር፣በዛሬው ሕይወትና በመጪው ዘላለማዊ ሕይወት የተድላና የደስታ መንገድ ተጓዝ። ይህን ስታደርግም በሕይወትህ ደስተኛ ትሆናለህና። ከሞትክ በኋላም ጌታህን ስትገናኝ የተረጋጋህና የታደልክ ትሆናለህና።

ፍጥረተ ዓለሙ በመላ እንዲሁ ለጌታው ተገዥና አምላኪ ነው። ሁሉም ፍጥረታት በየሁኔታቸው ጌታቸውን በማወደስ ያጠሩታል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ}[الجمعة: ١]،

‹‹በሰማያት ያለው በምድርም ያለው ሁሉ ለአላህ ንጉሥ ቅዱስ አሸናፊ ጥበበኛ ለኾነው ያሞግሳሉ።›› [አል ጁሙዓ፡1]

ከኃያልነቱ ፊትም ወድቀው ይሰግዳሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسۡجُدُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ وَٱلۡجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٞ مِّنَ ٱلنَّاسِۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيۡهِ ٱلۡعَذَابُ}[الحج: ١٨]،

‹‹አላህ በሰማያት ያለው ሁሉ፣በምድርም ያለው ሁሉ፣ፀሐይና ጨረቃም ፣ከዋክብትም፣ተራሮችም፣ዛፎችም፣ተንቀሳቃሾችም፣ከሰዎች ብዙዎችም፣ለርሱ የሚሰግዱለት መኾኑን አታውቁምን? ብዙውም በርሱ ላይ ቅጣት ተረጋገጠበት፤አላህ የሚያዋርደውም ሰው ለርሱ ምንም አክባሪ የለውም፤አላህ የሻውን ይሠራልና።››[አል ሐጅ፡18]

ይልቁንም እነዚህ ፈጥረታት እንደየአግባቡና እንደሁኔታቸው ለጌታቸው ይሰግዳሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلطَّيۡرُ صَٰٓفَّٰتٖۖ كُلّٞ قَدۡ عَلِمَ صَلَاتَهُۥ وَتَسۡبِيحَهُۥ}[النور: ٤١]،

‹‹አላህ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ፣በራሪዎችም ክንፎቻቸውን (በአየር ላይ) ያንሳፈፉ ኾነው፣ለርሱ የሚያጠሩ (የሚያወድሱ) መኾናቸውን አላወቅህምን? ሁሉም ስግደቱንና ማጥራቱን በእርግጥ ዐወቀ፤አላህም የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።››[አል ኑር፡41]

ከዚህ አስፈሪና አስደማሚ ትእይንት ኋላ ቀርተህ ተዋራጅ መሆን ለአንተ ተገቢ ነውን?! አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በማለት እውነት ተናግሯል፦

{أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسۡجُدُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ وَٱلۡجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٞ مِّنَ ٱلنَّاسِۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيۡهِ ٱلۡعَذَابُۗ وَمَن يُهِنِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِن مُّكۡرِمٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَفۡعَلُ مَا يَشَآءُ ١٨}[الحج: ١٨]

‹‹አላህ በሰማያት ያለው ሁሉ፣በምድርም ያለው ሁሉ፣ፀሐይና ጨረቃም ፣ከዋክብትም፣ተራሮችም፣ዛፎችም፣ተንቀሳቃሾችም፣ከሰዎች ብዙዎችም፣ለርሱ የሚሰግዱለት መኾኑን አታውቁምን? ብዙውም በርሱ ላይ ቅጣት ተረጋገጠበት፤አላህ የሚያዋርደውም ሰው ለርሱ ምንም አክባሪ የለውም፤አላህ የሻውን ይሠራልና።››[አል ሐጅ፡18]

https://www.path-2-happiness.com/am



አያስተነትኑምን?!

‹‹ወደ ሰማይ ተመልክቶ የተፈጥሮን ታላቅነት ካስተዋለ በኋላ በአላህ በማያምን ሰው በእጅጉ እደነቃለሁ።››

አብርሃም ሊንኮልን

የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት